# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 174 መስከረም 4 2004 ገጽ 1

**መለስና አሻንጉሊት ፓርላማው ኢትዮጵያዊ ድርጅቶችን እና ኢትዮጵያዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን የሚመዝኑበት መለኪያ አንድ አይደለም። በመለስ ፓርላማ አንድ ኢትዮጵያዊ ድርጅት "በሽብርተኝነት" ተፈረጀ ማለት ድርጅቱ 1. የመለስን አገዛዝ ስጋት ላይ ጥሎታል፣ 2. በርካታ ተከታዮች አሉት፣ እና ኢትዮጵያ ውስጥ ይንቀሳቀሳል ማለት ነው።**

**ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ለዚህ እውቅና በቅቷል።**

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

**ግዜ** ግንቦት 7 ዜና

## በስልጣን ላይ ያለውን ዘረኛና አምባገነን አገዛዝ ለማስወገድና ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት ኦነግ ከግንቦት7 እና ሌሎች ድርጅቶች ጋር በጋራ እንደሚሰራ አስታወቀ

ጥምረት ለፍትህ ለነጻነትና ለእኩልነት ባለፈው ቅዳሜ ጳጉሜ 3 ቀን በአሜሪካን አገር በዳላስ ከተማ አዘጋጅቶት በነበረው ስብሰባ ላይ ለተገኙት ኢትዮጵያዊያን ንግግር ያደረጉት የኦሮሞ ነጻነት ግምባር ዋና ጸሃፊ ፤ ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ በህዝባችን ላይ እያደረሰ ያለውን ሰቆቃ ለማስቆምና ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት ኦነግ ከግንቦት7 እና ለዲሞክራሲ ከሚታገሉ ሌሎች ድርጅቶች ጋር በጋራ ለመሥራት የሚያስችለውን ውይይት እያደረገ መሆኑን አስታወቀ።

የኦነግ ዋና ጸሀፊ አቶ አሚን ጁንዲ ጥምረት በዳላስ ቴክሳስ ባዘጋጀው ስብሰባ ላይ እንደተናገሩት ድርጅታቸው ከግንቦት7 ጋር በጋራ ለመስራት በመነጋገር ላይ እንደሆነ ገልጸው ለፍትህና ለነጻነት የሚታገሉ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ በመካከላቸው ያለውን ልዩነት ወደጎን ችላ አድርገው ሥልጣንን በሃይል ተቆጣጥሮ ባለው ዘረኛው ቡድን ላይ ብቻ እንዲያነጣጥሩ ጠይቀዋል።

በዚሁ ስብሰባ ኦነግ ኢትዮጵያንም ሆነ የኢትዮጵያን ህዝብ በጠላትነት ፈርጆ እንደማያውቅ የተናገሩት አቶ አሚን፣ በደርግና በዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ኦነግ አሉታዊ የሆነ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ስለተከፈተበት ምስሉ መበላሸቱን ከገለጹ ቦኋላ ኦነግ በኢትዮጵያ ውስጥ ዲሞክራሲያዊ ስርአት ተገንብቶ ማዬት እንደሚፈልግ ገልጸዋል። (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## የግንቦት7 ንቅናቄ ዶር ብርሃኑ ነጋ አዲሱ አመት በስልጣን ላይ ያለው ዘረኛ ተወግዶ ነጻና ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ የምትገነባበት እንዲሆን ጥሪ አቀረቡ

የግንቦት ሰባት ንቅናቄ ሊቀመንበር ዶር ብርሃኑ ነጋ በራሳቸውና በድርጅታቸው በግንቦት 7 ሥም ለኢትዮጵያዊያን ባስተላለፉት የአዲስ አመት መልእክት በስልጣን ላይ ያለው ዘረኛ አገዛዝ ተወግዶ ነጻና ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ የምትገነባበት እንዲሆን ጥሪ አቅርበዋል።

በተመሳሳይ መልኩ አንድነት ፓርቲ 2004 የለውጥ አመት እንዲሆን፣ ወጣቱ በአንድነት ለነጻነቱ እንዲነሳ ጥሪ አቅርቧል።

አንድነት ባወጣው በዚሁ መግለጫው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዘመናት የተነጠቀውን ነፃነቱን ለመቀዳጀት ዛሬውኑ ለትግል እንዲነሳ ጥሪ አቀርቡአል።ፓርቲው ለኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት በላከው መግለጫ እንዳመለከተው ወያኔ ኢህአዴግ የኢትዮጵያን ሕዝብ አፍኖ እየገዛ የሚቀጥልበት አንዳች ሞራላዊ ምክንያት የሌለው በመሆኑ፣ ይኸን አገዛዝ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሕጋዊና ሠላማዊ ትግል በማድረግ በቃህ ሊለው ሕዝቡም የስልጣኑ ባለቤት ሊሆን ይገባል፡ ብሎአል።

የ2004 ዓም እንዳለፉት ሃምሳ ዓመታት የጨለማ ዓመታት ሆኖ ሊቀጥል እንደማይገባው የገለጸው አንድነት፣ ለሁለንተናዊ ነፃነት ሁሉን አቀፍ የነፃነት ትግል የሚደረግበት አመት ሊሆን እንደሚገባው አሳስቦአል። በመጨረሻም አንድነት ለህዝቡ ባቀረበው ጥሪ ፡ በአሁኑ ወቅት በአረቡ ዓለም እየተካሄደ ያለው የነፃነት ትግልና ውጤቱም ተግባራዊ ተሞክሮውን እንዳጠናከረለት ገልጾ፣ ሕዝቡ ነፃ አውጭዎችን ቁጭ ብሎ የሚጠብቅበት ጊዜ በማብቃቱ እያንዳንዱ ሰው የነፃነቱ ባቤት ለመሆን አበክሮ ሊታገል እንደሚገባ ገልጿል፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ መድረክ ረሀብን ማጋለጥ በሽብርተኝነት ሊያስወነጅል እንደማይገባ መግለጫ ያወጣ ሲሆን፣ ጳጉሜ 4 ባወጣው በዚሁ መግለጫ ላይ እንዳመለከተው በተለይም በደቡብ የሃገራችን ክፍል የረሀቡ የአስከፊነት ደረጃው እየጨመረ ነው ካለ በሁአላ በቀን ሶስት ጊዜ እንመገብሃለን ብለው ያማለሉት ሕዝብ በረሃብ አለንጋ ሲገረፍ አገዛዙ በጠኔና በረሃብ መሃከል ያለውን ልዩነት ለማሳየት ሲዳክር መታየቱን አውግዟል። በመጨረሻም ወያኔ ኢሕአዴግ በወህኒ ያጎራቸውን የመድረክ አመራር አባላት፣ እንዲሁም ሌሎች የፖለተካ እስረኞችን ያላንዳች ቅድመ ሁኔታ ባስቸኳይ እንዲፈታ፣ የወያኔው አገዛዝ በኢትዮጵያ የተከሰውን ድርቅና ረሃብ ደብቆ ለሌሎች ችግር ደራሽ ለመምሰል የሚያደርገውን የገፅታ ግንባታ ጥረት አቁመው እውነታውን ያላንዳች መሸፋፈን ለዓለም ሕብረተሰብ ይፋ እንዲያደርጉ ጠይቋል።

የግንቦት 7 ሊቀመንበር ዶ|ር ብርሃኑ ነጋ ያስተላለፉት የአዲስ አመት መግለጫ ሙሉ ቃል በገጽ 3 ላይ ይመልከቱ።

## የአንድነት ፓርቲ ዋና ጸሃፊ አንዱአለም አራጌንና ታዋቂውን ጋዜጤኛ እስክንድር ነጋን ጨምሮ አምስት ኢትዮጵያዊያን ታሠሩ፣ ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ባወጣው መግለጫ ኢትዮጵያዊያኑ የታሰሩት ከግንቦት ሰባት ንቅናቄ ጋር ግንኙነት ስላላቸው ነው ተብሎአል

ያለህዝብ ፈቃድ ለዘመናት ሥልጣን ላይ ሆነው የህዝብና የአገራቸውን ደም የሚመጡ አምባገነኖችን የሥልጣን መሠረት እያናጋ የመጣው የሰሜን አፍሪካ ህዝባዊ አብዮት ያስደነገጠው የወያኔ አገዛዝ፤ ተመሳሳይ ህዝባዊ አመጽ ሊቀሰቀስብኝ ይችላል ከሚል ስጋት በአገር ውስጥ ተመዝግበው ሠላማዊ ትግል ለማካሄድ የሚንቀሳቀሱትን የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት መሪዎችና፣ የዲሞክራሲ አክትቪስቶችን በገፍ ማሰር እንደቀጠለ የግንቦት 7 ዜና ዘጋቢ ከአዲስ አበባ በላከልን ዜና አስታወቀ። እንደዘጋቢያችን ሪፖርት ባለፈው ረቡዕ መስከረም 3 ቀን የአንድነት ፓርቲ ዋና ጸሃፊ አንዱአለም አራጌንና ታዋቂውን ጋዜጤኛ እስክንድር ነጋን ጨምሮ አምስት ኢትዮጵያዊያን የታሠሩ፣ ሲሆን፣ ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ባወጣው መግለጫ ኢትዮጵያዊያኑ የታሰሩት ከግንቦት ሰባት ንቅናቄ ጋር ግንኙነት ስላላቸው ነው ማለቱን ዘጋቢያችን የላከልን ሪፖርት ያመለክታል።

የኦሮሞ ፌደራሊስት ንቅናቄና የኦሮሞ ኮንግረስ ደጋፊዎችና አባላት ላይ ከሁለት ሳምንት በፊት የተጀመረው ይህ የጅምላ እስር በተጠናከረ መልኩ ቀጥሎ፣ በ60 ዎቹ የ ዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኘውን አርቲስት ደበበ እሼቱን በታሠረ ሳምንት ዕድሜ ውስጥ የአንድነት ፓርቲ ዋናጸሃፊ የሆኑት አቶ አንዱአለም አራጌ፤ ታዋቂው ጋዜጤኛ እስክንድር ነጋ፣ ዘመኑ ሞላ፣ ናትናኤል መኮንንና አሳምነው ብርሃኑ በአረመኔው አገዛዝ ታስረዋል። (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## በመስከረም ወር አዲስ አበባ ውስጥ የደረሰውን ፍንዳታ ያቀነባበረውና የፈጸመው ሽብርተኛው የወያኔ አምባገነን አገዛዝ እንደነበር ዊኪሊክስ አጋለጠ

መስከረም ወር ላይ በአዲስ አበባ ከተማ ለሶስት ሰዎች ህይወት ማለፍ ምክንያት የሆነውንና በርካታ ንብረት ያወደመውን የቦምብ ፍንዳታ ያቀነባበረውና ሴራውንም የሸረበው ዘረኛውና አጥፊው የወያኔ አገዛዝ ቁንጮ መለስ ዜናዊ እንደነበር በዊኪ ሊክስ ላይ አፈትልኮ የወጣው የአሜሪካ መንግሥት መረጃ አጋለጠ።

በወቅቱ በአዲስ አበባ ፍንዳታ በደረሰበት ወቅት ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ በቁጥጥሩ ስር በሚገኙት የቴሌቪዥንና ራዲዮ ጣቢያዎች ፍንዳታውን የፈጸሙት የኦሮሞ ነጻነት ግምባር ሽብርተኞች ናቸው በማለት በርካታ ኢትዮጵያዊያንን ወደ እስር ቤት ማስገባቱና ማሰቃየቱንም ዊኪሊክስ አክሎ ገልጹአል።ይሁን እንጂ ከአሜሪካን ኤምባሲ አፈትልኮ የወጣው መረጃ እንደሚያመለክተው፣ ፍንዳታውን ያቀነባበረውና ቦምቡንም እንዲፈነዳ ያደረገው ራሱ የወያኔ አገዛዝ ሳይሆን እንደማይቀር መግለጹ ታውቁአል።

በአዲስ አበባ ከተማ በካራቆሬ ክፍለ ከተማ የደረሱትን ሶስት ተከታታይ ፍንዳታዎች በሚመለከት ቦምቡን ያጠመዱትም ሆነ ያፈነዱት የኢትዮጵያ በዲሞክራሲያዊ ጎዳና መገስገስና በልማት መበልጸግ የሚያንገበግባቸው ሽብርተኞች ናቸው በማለት የዘረኛው አገዛዝ ባለስልጣናት ሪፖርት አድርገው እንደነበር ዊኪሊክስ አጋልጦአል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ዘረኛው እና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ የሱዳን ፕሬዝዳንት አልባሽር ላይ መፈንቅለ መንግሥት ሴራ ማስተባበሩን በማስተባበል እርስ በርሱ የሚቃረን መግለጫ አስወጣ

በምሥራቅ አፍሪካ ቀንድ ያለው የጸጥታ ስጋት እስካለ ድረስ ምዕራባዊያን ለወያኔ አገዛዝ የሚያደርጉት ያልተገደበ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ድጋፍ እንደማይቋረጥበት የተገነዘበው የፋሽስቱ መለስ ዜናዊ ቡድን፤ አሜሪካኖች የሱዳኑን ፕሬዝዳንት ጀኔራል አልባሽርን ከሥልጣን ያስወግዱ ዘንድ ብላሃት ማቀበሉን ከአሜሪካ ውጪጉዳይ መሥሪያቤት ሾልኮ በዊኪሊክስ መረጃ ድሬገጽ ላይ የወጣው ሠነድ ካጋለጠ ወዲህ የወያኔ የኮሚኒኬሽን ኤጀንሲና የወጪ ጉዳይ ሚንስትር መረጃውን ለማስተባበል ደፋ ቀና እያሉ መሆኑን ለማወቅ ተችሎአል።

ከትናንትና ወዲያ ሃሙስ መስከረም 3 ቀን አገዛዙ ባወጣው የማስተባባያ መግለጫ መለስ ዜናዊ የሱዳኑን ፕሬዝዳንት ከሥልጣን ለማስወገድ ስለሚቻልበት ሁኔታ ከአሜሪካ ባለሥልጣናት ጋር አድርጎት የነበረውን ውይይት ሙልጭ አድርጎ ከመካዱም በላይ ቅሌቱን ያጋለጠውን መረጃ አዲስ አበባ የሚገኘው የአሜሪካ ኤምባሲ አዛብቶ ያስተለለፈው የሃሰት ወሬ ነው በማለት የተለመደውን ቅጥፈቱን አስነብቦአል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## በመለስ ዜናዊ “ሽብርተኛ” መባል የአርበኝነት ሜዳሊያ ሆኗል

ለገዛ ራስና ለሃገር ነፃነት አርበኛ መሆን በመለስ ዜናዊ እና እሱ በሚቆጣጠራቸው ሚዲያዎች “ሽብርተኛ” ያስብላል፤ ያስከስሳል፤ ያሳስራል።

አርበኝነት ክብር ነው። አርበኝነት የመልካም ዜግነት ከፍተኛው መገለጫ ነው። አርበኝነት የታላቅ ስብዕና መገለጫ ነው። በመለስ ዜናዊ እና እሱ በሚቆጣጠራቸው ሚዲያዎች “ሽብርተኛ” መባል የአንድ ኢትዮጵያዊ ግለሰብ ወይም ኢትዮጵያዊ ድርጅት አርበኝነት ማሳያ ሆኗል። እናም በመለስ ዜናዊ “ሽብርተኛ” መባልና የሚያኮራና የሚያስደስት ነገር ሆኗል።

መለስ ዜናዊ “ሽብርተኛ” እያለ የሚጠራቸው ኢትዮጵያዊያን ግለሰቦች-

1. ዘረኝነትን የሚቃመው፣
2. ለሰብዓዊ መብቶች ልዕልና ጥብቅና የቆሙ፣
3. ለኢትዮጵያ ዘላቂ ልማትና እድገት ብሩህ ራዕይ ያላቸው፣
4. የህዝብ አመኔታና ፍቅር የተቸራቸው፣ እና በሙያቸውም የተከበሩ

ዜጎች መሆናቸው በተደጋጋሚ ታይቷል። በመለስ አንደበት “ሽብርተኛ” መባል የአንድን ኢትዮጵያዊ ታላቅነት ማሳያ ሆኗል።

ወጣቶቹ ጋዜጠኞች ውብሸት ታዬ እና ርዕዮት ዓለሙ በለጋ እድሜዓቸው በመለስ ዜናዊ “ሽብርተኛ” የመባልን ክብር ተቀዳጅተዋል። በመለስ አገዛዝ “ሽብርተኛ” መባላቸው ብቻውን ስለ ውብሸትና ርዕዮት ታላቅነት ብዙ ይናገራል። በርካታ ኢትዮጵያዊያን ወጣቶች በውብሸትና ርዕዮት መንፈሳዊ ቅናት አድሮባቸዋል።

አቶ በቀለ ድሪባ፣ አቶ አልባና ሌሊሳ እና በርካታ ሌሎች ቆራጥ ኢትዮጵያዊያን ለመለስ ዜናዊ “የሽብርተኝነት”፤ ለኢትዮጵያ ህዝብ ደግሞ የአርበኝነት ኒሻን በቅተዋል።

ሰሞኑን ደግሞ አዛውንቱ አርቲስት ደበበ እሸቱ ለዚህ ታላቅ ክብር መብቃቱ መለስ ዜናዊ መስክሮለታል። ይህ ደግሞ ለአርቲስቱ ቀድሞውኑ በነበረው ክብር ላይ ተጨማሪ ካባ ደርቦለታል።

በድርጅቶችም ቢሆን እንደዚያው ነው።

መለስና አሻንጉሊት ፓርላማው ኢትዮጵያዊ ድርጅቶችን እና ኢትዮጵያዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን የሚመዝኑበት መለኪያ አንድ አይደለም። በመለስ ፓርላማ አንድ ኢትዮጵያዊ ድርጅት “በሽብርተኝነት” ተፈረጀ ማለት ድርጅቱ

1. የመለስን አገዛዝ ስጋት ላይ ጥሎታል፣
2. በርካታ ተከታዮች አሉት፣ እና ኢትዮጵያ ውስጥ ይንቀሳቀሳል ማለት ነው።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ለዚህ እውቅና በቅቷል።

ግንቦት 7 አሁን ባገኘው እውቅና ሳይኩራራ መለስ ዜናዊንና መላውን አገዛዙን ከዚህም በላይ አስጨንቆና አስገድዶ ከኢትዮጵያ ጫንቃ ላይ ለማውረድ ተግቶ ይሰራል።

የመለስ ዜናዊ “የፀረ-ሽብርተኝነት” አዋጅ የኢትዮጵያን ህዝብ ይበልጥ ያስቆጣል፤ ይበልጥ ያነሳሳል እንጂ ማስፈራራት አይችልም።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

## አረመኔው የወያኔ አገዛዝ የጸረ ሽብርተኝነት ህጉን ህጋዊና ሰላማዊ ተቃውሞን ለማፈኛ እያዋለው ነው ሲል አንድነት መግለጫአ አወጣ

በፍርሃት ሽምቀቅ ውስጥ ገብቶ እንደቆሰለ አውሬ ያገኘውን ሁሉ በመናከስ ያለው አምባገነን የወያኔ አገዛዝ የአንድነት ፓርቲ ም/ል ሊቀመንበርና የህዝብ ግንኙነት ሀላፊን እንዲሁም የሌሎችንም የፓርቲውን ከፍተኛ አመራሮች ማሰሩን አስመልክቶ የፓርቲው አመራር አካላት በትናንትናው እለት በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ እንደገለጹት፣ የአቶ አንዱአለም አራጌ፣ የአቶ ናትናኤል መኮንን፣ የአቶ አሳምነው ብርሀኑ እና የጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ መታሰር፣ ዘረኛው ወያኔ የጸረ ሽብርተኝነት ህጉን ህጋዊና ሰላማዊ ተቃውሞን ለማፈኛ እያዋለው መሆኑን ያመለክታል ብለዋል።

የአንድነት የፓርቲ አመራሮች በመግለጫቸው እንደጠቀሱት ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በአንድነት ፓርቲ ላይ በሽብርተኛ ስም ጥቃት የሰነዘረበት ፓርቲው እየተጠናከረና የህዝብ አመኔታን እያገኘ በመምጣቱ ነው ብለዋል።

እንደ አንድነት መግለጫ ወያኔ በእነ አቶ አንዱአለም ላይ የወሰደው እርምጃ በተቃዋሚ ፓርቲዎች ውስጥ ከፍተኛውን አመራር እየያዙና ብቃታቸውን እያስመሰከሩ የመጡትና እየመጡ ያሉትን ወጣቶች ከትግል ሜዳው በማሸሸት፣ በእንጭጩ ለማስቀረት መሆኑም አመራሮቹ መናገራቸው ተገልጹአል።

አንድነት በመግለጫው መጨረሻም ህዝቡ ለመብቱና ለነጻነቱ መከበር በመታገል ትግሉን ሊቀለበስ ወደ ማይችልበት ደረጃ የማድረስ ሀላፊነቱን እንዲወጣ ጥሪ አቅርቦአል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ዜና ዘረኛው አገዛዝ በሽብር ድርጊት ጠርጥሬያቸዋለሁ ብሎ በፌዴራል ፖሊስ በቁጥጥር ሥር ያዋላቸውን ጋዜጠኛና የፖለቲካ ፓርቲ የአመራር አባላትን ሀሙስ እለት ፍርድ ቤት እንዳቀረባቸው ተያይዞ የደረሰን ዜና አምለክቱአል፡፡ ታዋቂው ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ፣ የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ምክትል ሊቀመንበርና የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አንዷለም አራጌ፣ የመላው ኢትዮጵያን ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ /መኢዴፓ/ ዋና ጸሐፊ አቶ ዘመኑ ሞላ፣ የአንድነት ፓርቲ አባላት የሆኑት አቶ ናትናኤል መኮንን እና አቶ አሳምነው ብርሃኑ ሀሙስ ከቀኑ 9፡00 እስከ 11፡00 ሰዓት ድረስ በአራዳ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ችሎት እንደቀረቡ ታውቁአል፡፡

በዘረኛውና አረመኔው አገዛዝ በሽብር ተግባር የተወነጀሉት አምስት ግለሰቦች በተናጥል ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ የተደረገ ሲሆን ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋን በችሎቱ በመጀመሪያ እንዲቀርብ ያደረገው የፌዴራል ፖሊስ ማንም ሰው ወደ ችሎቱ እንዳይገባ ሆን ብሎ በማገዱ የእስክንድር ቤተሰቦች፣ ጋዜጠኞችና ሌሎች ሰዎች የክስ ሂደቱን ሳይከታተሉ ቀርተዋል፡፡

በሁለተኛው ግለሰብ ችሎት ላይ የታሳሪ ቤተሰቦችና ጋዜጠኞች ጭሀትና ብሶታቸውን በመግለጻቸው ችሎቱ ክፍት እንዲሆን የተደረገ ሲሆን፣ የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ምክትል ሊቀመንበርና የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ አንዷለም አራጌ ክሱን እንዲከላከል ሲጠየቅ፡- ወያኔ በአሁኑ ጊዜ በግልጽ የአፈና ሥራ እየሰራ ነው፣ እኔ ምንም ወንጀል አልሰራሁም በአንፃሩ እኔ ላይ አገዛዙ ወንጀል እየሰራብኝ መብቴን የሚያስከብርልኝ አካል ስላጣሁ፣ ይህ ፍርድ ቤትም በነፃነት ይሰራል የሚል እምነት ስለሌለኝ እስከ ሞት ፍርድ ድረስ የፈለጋችሁትን ልታደርጉኝ ሁሉ በእጃችሁ ነውና የፈለጋችሁትን ወስናችሁ ልታስታዉቁኝ ትችላላችሁና አልከላከልም” ብሏል፡፡ በችሎቱ ላይ ፖሊስ ለተጨማሪ ምርመራ ጊዜ ያስፈልገኛል በማለቱ ፍርድ ቤቱ 28 ቀን የጊዜ ቀጠሮ ሰጥቶ ለጥቅምት 2 ቀን 2004 ዓ.ም ተቀጥሯል፡፡

የጋዜጠኛ እስክንድ ነጋ ባለቤት ጋዜጠኛ ሠርካለም ፋሲል በከረንት አፌይርስ የመወያያ ክፍል ባደረገችው አጭር ቃለ ምልልስ፣ ረቡእ ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት ላይ ልጃችንን ከትምህርት ቤት በማምጣት ላይ ሳለ ነበር እስክንድርን ከመንገድ የያዙት፣ በጊዜው ደውሎ መያዙን ነግሮኝ የ5 ዓመት ህጻን ልጃችንን ለእኔ እስኪያስረክበኝ እንኳ አልጠበቁትም እጁ ላይ ካቴና ሲያስገቡ፣ እኔ ስደርስ ልጃችን መሬት ወድቆ ያለቅስ ነበር ብላለች፡፡ በተጨማሪም ለኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ረቡእ ወደ 11፡30 ሰዓት አካባቢ ላይም ወደ 15 የሚጠጉ ፖሊሶችና ሲቭል ለባሾች ወደ ቤታችን መጥተው በመበርበር እስክንድር የፃፋቸውን ወረቀቶች፣ ሲዲዎችና ላፕቶፕ ኮምፒውተር ይዘው ሄደዋል ብላለች፡፡

## አንድ የጀርመን ፓርላማ አባል በኢትዮጵያ ያለዉ የሰብአዊ መብት አያያዝ እጂግ አሳሳቢ ሆኑአል አሉ

የህገሪቱን ሠላምና ፀጥታ ለማደፍረስና ሕገ-መንግሥታዊዉን ሥርዓት ለማፍረስ አሲረዋል በማለት የዘረኞች ቁንጮ መለስ ዜናዊ አገዛዝ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትንና ጋዜጠኞችን በሽብርተኝነት ስም በማሰር የጀመረዉ ዘመቻ እጅግ እንዳሳሰባቸዉ የጀርመን ፓርላማ አባል ቲሎ ሆፐ ገለፁ።

እንደ ፓርላማ አባሉ መግለጫ የአረመኔው መለስ አገዛዝ በመዉሰድ ላይ ያለዉ እርምጃ በወያኔ አገዛዝ ላይ የሰላ ሂስ የሚሰነዝሩ ሃይሎችን ስልታዊ በሆነ መንገድ ለማጥፋት ሊሆን ይችላል ብለው እንደሚያምኑ ተናግረዋል።

ካለፈዉ መጋቢት ጀምሮ ቁጥራቸዉ 370 የሚሆኑ የፖለቲካ ተቃዋሚዎች የታሰሩ ሲሆን ከነዚህም ዉስጥ 217 የሚሆኑት የኦሮሞ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ / ኦፍዴን/ አባላት እንደሆኑ ቲሎ ሆፐ ጠቅሰዋል። በቀለ ገርባ፤ አልባና ሌሊሳ፤ እንዲሁም አርቲስት ደበበ እሼቱን ተከትሎ የጋዜጠኛ እስክንድር ነጋና የአንድነት ለፍትህና ለዲሞክራሲ ዋና ፀሃፊና የህዝብ ግንኙነት ሃላፊ የሆኑት የአንዱአለም አራጌ እና ሌሎችም በተከታታይ በሽብርተኝነት እየተወነጀሉ እስር ቤት መጣላቸዉ አጅግ አሳሳቢ እንደሆነ ተናግረዋል።

የጀርመን መንግስት ድርጊቱን በጥብቅ በማዉገዝ ለኢትዮጵያ መንግሰት ባለስልጣኖች ጠንካራና ግልፅ አቋሙን ማሳወቅ እንደሚገባዉ የገለፁት የፓርላማ አባል መንግስታቸዉ እስረኞቹ እንዲፈቱ እንዲጠይቅና ይህን መሰሉ የሰብአዊ መብት ጥሰት በሁለቱ አገሮች የልማት ትብብር ላይ ተጽእኖ እንደሚኖረዉ በግልፅ ማስታወቅ እንዳለበት አሳስበዋል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ የወያኔው አገዛዝ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትንና ጋዜጠኞችን በአሸባሪነት ጥርጣሬ ማሰሩን አለም አቀፉ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅት አምንስቲ ኢንተርናሽናል መቃወሙ ታዉቋል።

በድርጅቱ የኢትዮጵያና ምሥራቅ አፍሪካ ጉዳይ አጥኚ ክሌር በስተን በለንደን ከጀርመን ድምፅ ወኪል ጋር ባደረጉት ቃለ መጠይቅ የኢትዮጵያ መንግሥት ሰዎችን በአሸባሪነት ስም የሚያስረዉ የፖለቲካ ፓርቲዎች፥ የመብት ተቆርቋሪ ተቋማትና ጋዜጠኞች የሚያሰሙትን ቅሬታና ተቃዉሞ ለማፈን እንደሆነ የዶቼቬሌ ሬዲዮ የአማርኛዉ ገልጿል። ዘረኛው አገዛዝ የእስረኞቹን ሕጋዊ መብት እንዲያከብርም ክሌር በስተን ጠይቀዋል።

ይህ በዚህ እንዳለ በኢትዮጵያ ውስጥ እየከፋ በመጣው የሰብ አዊ መብት ጥሰት ምክንያት 15 አትሌቶች በሞዛምቢክ በመደረግ ላይ ባለው የአፍሪካ ጨዋታዎች ውድድር ላይ ሲሳተፉ ከቆዩ በሁዋላ መሰወራቸውን ቢቢሲ ዘግቦአል። አትሌቶቹ ስላሉበት ሁኔታ የአገሪቱ መንግስት እንደማያውቅ የገለጸ ቢሆንም የአትሌቶቹ አሰልጣኝ ወደ ደቡብ አፍሪቃ ሳይጉአዙ እንዳልቀረ መግለጹም ተዘግቡአል።

# የግንቦት 7፡ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የአዲስ ዓመት መልዕክት

## የግንቦት 7 ሊቀመንበር ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ያስተላለፉት የአዲስ አመት መግለጫ ሙሉ ቃል

ውድ የኢትዮጵያ ህዝብ!

በቅድሚያ በግንቦት 7፡ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ እና በራሴ ስም "እንኳን ከዘመን ወደ ዘመን አሸጋገረን" እላለሁ።

ያሳለፍነው 2003 ዓመተ ምህረት በዓለም ላይ ብዙ አስደናቂና ተስፋ ሰጪ ኩነቶች የታዩበት ዓመት ነበር። እኛ በነፃነት ስንኖር በቅኝ ግዛት ባርነት ውስጥ ይኖሩ የነበሩ ብዙ አፍሪካዊ ወገኖቻችን እኛን አልፈው ሄደው ከራሳቸው አምባገነኖች ተላቀው የነፃነት አየር እየተነፈሱ ነው። እንደኛው በአምባገነን አገዛዞች ሲረገጡ የነበሩ የሰሜን አፍሪቃና የመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች ህዝቦች አምባገነንነትን ተራ በተራ ከጫንቃቸው ሲያስወግዱ አይተናል፤ ቱኒዝያ፣ ግብጽና ሊቢያ የተቀጣጠለው የነፃነት ሰደድ ወላፈኑ እኛም አገር ደርሷል።

የመለስ ዜናዊ አገዛዝም ይህንኑ በቅጡ በመረዳቱ መወራጨቱ በዝቷል። አንዴ ከየት እንደመጣ ባልታወቀው በአባይ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት፤ በሌላ ጊዜ ደግሞ "በትራንስፎርሜሽን" ወሬ ሊያማልለን ቢሞክርም የህዝቡን ትኩረት ለመሳብ ግን አልቻለም። እሱ ግን እያስገደደ ከህዝቡ ገንዘብ መዝረፉን እንደቀጠለበት ነው።

በሃገራችን በደልና ምሬት በዝቷል። ድህነትና ጉስቁልና ከመቸውም በባሰ ተንሰራፍቷል። እስርና ሰቆቃ (ቶርቸር) ተራ ነገሮች ሆነዋል። በአሸባሪዎች ስም በከተማችን የሚፈነዱት ቦምቦች የመለስ ደህንነቶች ሆን ብለው ያጠመዷቸው ቦምቦች መሆናቸውን ዓለም እየመሰከረም፤ ሰላማዊ ዜጎች በአሸባሪነት እየተፈረጁ ለስቃይ መዳረጋቸው የዘወትር የመለስ ዓይን አውጣ ትዕይንት ሆኗል። ዛሬ በሃገራችን አርሶ መኖር አይቻልም፤ ሰፋፊውና ለሙ መሬት ለባዕዳን ቱጃሮች ተሰጥቷል። ነግዶ፣ ቸርችሮ ማደርም አይቻልም። የባንክ ብድር እንደፈለጉና በርካሽ ከሚያገኙ፤ ግብርና መዋጮ ከማይከፍሉ የወያኔ የንግድ ድርጅቶች ጋር ተፎካክሮ፤ ለከት ያጣ ግብርና መዋጮ ከፍሎ ማትረፍ አይታሰብም።

ኑሮ እጅግ በመወደዱ ወያኔ በጠላትነት የፈረጀው ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች የሚደልላቸው የገዛ አባላቱ እንኳን ሳይቀሩ ቤተሰቦቻቸውን ከረሃብ መታደግ አልቻሉም። አብዛኛው ዜጋ ልጆቹን በቀን አንድ ጊዜ እንኳን መመገብ ተስኖታል።

የወጣቶች ተስፋ የጨለመ በመሆኑ ተረጋግተው ትምህራቸውን መከታተል አልቻሉም። ትምህርቱ ራሱ አለ ማለትም አይቻልም።

በተገኘው መንገድ ሁሉ ከዚህ ስቃይ ለመሸሽ በርካታ ወገኖቻችን በጀልባዎች ወደ አረብ አገራት ለመሻገር ሲሞክሩ ሰጥመው የባህር አውሬዎች ቀለብ ሆነዋል። ሌሎች ደግሞ በእግር ጉዞ በረሃ ሲያቋርጡ በሃሩር ደርቀው ቀርተዋል። የጎረቤቶቻችን አገሮች እስር ቤቶች የሞሉት በኢትዮጵያዊያን ወጣት ወንዶችና ሴቶች ነው። ኢትዮጵያዊያን ወጣቶች በአገራቸው ያለውን ሰቆቃ ለማምለጥ ሲሞክሩ፤ በሊቢያ በፈላ ውሀ ስትለበለብ እንደከረመችው እህታችን ሽዋዩ ሙላ፤ በጎረቤት አገራት ሰቆቃ ውስጥ ገብተዋል።

በአንፃሩ ደግሞ የዘመኑን ባለባቶች የተንቀባረረ ኑሮ ማየት ያበግናል። እነሱ በዘረፉት ገንዘብ ፎቆችና ቪላዎችን እየገነቡ ይዝናናሉ። እነሱ ለቁጥር የሚያታክት ገንዘብ ወደ ዉጭ አገራት ያሸሻሉ። እነሱ ለድሃው የመጣውን እርዳታ ተከፋፍለው ብሉና ብላክ ሌብል፤ ውስኪና ሻምፖኝ ይራጩበታል። ጣእሙን በቅጡ የማያውቁትን ካቪያርን ውድ ስለሆነ ብቻ የውስኪ ማወራረጃቸው አድርገውታል።

አገራችንና ህዝቧ የረሃብ የስቃይና የውርደት አዙሪት ውስጥ ናቸው። የመለስ አገዛዝ ካልተወገደ በስተቀር አገራችንና ህዝባችን ከረሃብ፣ ከድህነትና ከውርደት መውጣት አይችሉም። የመለስ ዜናዊ እኩይ አገዛዝ ከዚህ በላይ እንዲቆይ ከፈቀድንለት ሁላችንም የጋሻጃግሬዎቹና የባዕዳን ሸሪኮቹ የቀን ሠራተኞች መሆናችን አይቀርም። የቅጥራችን እና የኑሯችን ሁኔታም ከባርነት የባሰ እንጂ የተሻለ እንደማይሆን እያየነው ነው።

ውድ የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ!

ነፃነት መኖሩን እያወቅን ባርነትን መቀበል አይቻለንም!!! የመለስ ዜናዊን አገዛዝ ማስወገድ አሁን እየደረሰብን ካለው መከራ የከበደ ነገር አይደለም። ባህር በታንኳ ለመሻገር፤ በረሃን በእግር ለማቋረጥ የቆረጠ ወጣት ራሱን ነፃ አውጥቶ የስደትን ስቃይና ውርደት ማስቀም እንደሚችል ጥርጥር የለኝም። ከቅኝ ገዢዎች ወረራ ራሱን ለመከላከል ከፍተኛ መስዋእትነት በመክፈል ነፃነቱን አስከብሮ የኖረ ህዝብ በመለስ ዜናዊ ጋባዥነት ባዕዳን ሃገሩን እየተቀራመቱት ክርስቱና ከቀየው እየነቀሉ ክብር-አልባ ሃገር-አልባ እያደረጉ አንገዋለው ሲጥሉት "በቃ!" የማለት፤ "እምቢ!" የማለት ጀግነነት በደሙ አሁንም እንደሚፈስ ጥርጥር የለኝም። የመለስ ዜናዊ አገዛዝን እብሪት፣ ዘረኛነትና ዘረፋ ህሊናችን ፈጽሞ ሊቀበለው የሚገባ ጉዳይ አይደለም።

በደል በዝቷል። ምሬት በዝቷል። ሆኖም መፍትሄ መሻት እንጂ የደረሱብንን በደሎች መዘርዘር ፋይዳ የለውም።

ወገኖቼ !!!!

ከዚህ በላይ በዚህ ማጥ ውስጥ መቆየት አንችልም። የመለስ አገዛዝ መወገድ ይኖርበታል!!! ይህ ደግሞ በአስቸኳይ ሊፈፀም የሚገባው ተግባር ነው!!!

አዲሱን ዓመት የመለስ ዜናዊ ግፈኛና ዘረኛ አገዛዝ ተወግዶ የብሩህ ተስፋ መንገዳችንን የምንጀምርበት ዓመት ማድረግ ይገባናል። ይህ አዲስ ዓመት ይዞ የመጣልን መልካም እድሎች ሊያመልጡን በፍጹም አይገባም።

አዲሱን ዓመት እንደተቀበልን የምናመራው በድል መጠናቀቅ ወደሚኖርበት ሁለገብ ትግል ነው። ይህ ትግል ለነፃነት፣ ለእኩልነት፣ ለፍትህ፣ ለዴሞክራሲ፣ ለሰላምና ለአንድነት የሚደረግ ትግል ነው። ይህ ትግል ቸነፈርን በብልጽግና፤ ውርደትን በክብር ለመተካት የሚደረግ ትግል ነው።

ይህንን ትግል በአሸናፊነት መወጣት የህልውና ጉዳይ ነው። ወገባችን አስረን፤ ሃሞታችንን አስቆጥተን እንነሳ!!!

**ብርሃኑ ነጋ ነኝ**

**አዲሱን ዓመት የነፃነት ዓመት ያድርግልን!!!!!**

### በስልጣን ላይ ያለውን ዘረኛና አምባገነን አገዛዝ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የዘረኛው መለስ አገዛዝ እስከዛሬ በስልጣን ላይ ሊቆይ የቻለው ኢትዮጵያውያን አንድ ሆነው ለመተባበር ባለመቻላቸው መሆኑን የገለጹት አቶ አሚን አኑኅ እስከዛሬ የተደረገውን ትግል ገምግሞ፣ ለዘላቂ ሰላም፣ ፍትህና ዲሞክራሲ ቁርጠኛ ውሳኔ መወሰኑን ገልጸዋል።

አኑኅ በስልጣን ላይ ያለውን አገዛዝ አስወግዶ ዲሞክራሲያዊ ስርአት መገንባት የሚቻለው ትብብር በመመስረት ብቻ መሆኑን እንደሚያምን፣ ይህን ትብብር ለመመስረት ደግሞ ሁላችንም የግድ አንድ ቋንቋ፣ አንድ እምነትና አንድ አመለካከት መያዝ የለብንም ሲሉ ዋና ጸሀፊው ገልጸዋል።

በሌላም በኩል የግንቦት 7 ንቅናቄ ዋና ጸሃፊ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ በበኩላቸው መተባበር ሳንችል ቀርተን፣ አገራችንን እንዲያወድም ከፈቀድን ማናችንም ከተጠያቂነት አንድንም፣ ታሪካችንን አውቀን፣ መጥፎ ታሪካችን እንዳይደገም ዘግተን፣ መጻኢውን ታሪክ እየጻፍን መጓዝ እንዳለብን ልንገነዘብ ይገባል በማለት ተናግረዋል። በመጨረሻም አቶ አንዳርጋቸው ከኦኑኅ ጋር የሚደረገው ንግግር ለሁሉም ኢትዮጵያ የምትመች አገር ለመፍጠር መሆኑን ተናግረዋል።

### የአንድነት ፓርቲ ዋና ጸሃፊ አንዱአለም አራጌንና ታዋቂውን ጋዜጤኛ እስክንድር ነጋን . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የወያኔ አገዛዝ በአገሪቱ ውስጥ ከዕለት ወደ ዕለት እየከፋ ለመጣው የኑሮ ውድነት መላ እንዲያበጅለት በሠላማዊ ሠልፍ ለመጠየቅ ለመስከረም 21 ቀን የሠልፍ ፈቃድ የጠየቀው የመላው ኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ ምክትል ፕሬዝዳንትም ከታሳሪዎቹ አንዱ እንደሆኑና በወያኔ የጸጥታ ሰዎች ታፍነው እንደተወሰዱ ታውቋል።

ለወያነ የደህንነት ምንጮች ቅርበት ያላቸው የንቅናቄያችን መረጃ ምንጮች ለዝግጅት ክፍላችን እንዳስታወቁት ይህ የጅምላ እሥር እርምጃ የተጀመረው የህወሃት ፖሊት ቢሮ በአገራችን ውስጥ ህዝባዊ አመጽ መፈንዳቱ አይቀሬ መሆኑን መረጃ ካሰባሰበ በኋላ፤ ተቃውሞ ሊያደራጅ ወይም ሊቀሰቅስ የሚችል ማንኛውንም አይነት እንቅስቃሴ በ ዕንጪጩ ለማምከን እርምጃ እንዲወሰድ በምስጥር ባደረገው ስብሰባ ውሳኔ ካስተላለፈ ከቀናት ቦኋላ እንደሆነ ታውቋል።

እንደመረጃ ምንጮቻችን አመጽ ለማምከን መወሰድ ስላበት እርምጃ በህወሃት ውስጥ ውይይት በተደረገበት ወቅት የሶሪያው መሪ ሃሰን አላሳድ ተቃውሞ ለማፈን እየተጠቀመበት ያለው አይነት እርምጃ መውሰድ አዋጭ ነው የሚል ነጥብ ተነስቶ እንደነበር ለማወቅ ተችሎአል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የኢትዮጵያ አንድነት ዲሞክራሲያዊ ድርጅት(ኢአዴድ) እና የመላው ኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ (መኢዴፓ)፤ መስከረም 21 ቀን ለማካሄድ ያቀዱትን ሰልፍ አስመልክቶ ጋዜጣዊ መግለጫ መስጠታቸውን ኢሳት ዘግቦአል።

እንደ ኢሳት ዘገባ የፓርቲዎቹ መግለጫ የሰልፉ ዋነኛ አላማ፤ ድህነትንና የኑሮ ውድነትን ጨምሮ በተለያዩ ዘርፎች አገራችንን አስረው ለያዟት ማነቆዎች ዋነኛ ምክንያት የሆነውን የወያኔ ፓርቲ ፖሊሲና አሠራር አጥብቆ መቃወም ነው ተብሎአል።

የፈቃድ ጥያቄ የገባለት የአዲስ አበባ መስተዳድር የህዝባዊ ስብሰባና ሰልፍ ፈቃድ ክፍል እስካሁን ምላሽ ባይሰጣቸውም፣ ወያኔ አለኝ በሚለው ህገ-መንግስት ሰልፍና ስብሰባ ለማከናወን ማሳወቅ ብቻ በቂ እንደሆነ ፓርቲዎቹ አስታውሰዋል።

ከጧቱ 3፡00 ሰዓት እስከ ቀኑ 8፡00 ሰዓት ድረስ በሚቆየው የ5 ሰዓታት ሰልፍ፤ እጅግ በርካታ ሰዎች በመውጣት ብሶታቸውን ያሰማሉ፤ በስርዓቱ ላይ ያላቸውንም ተቃውሞ ይገልፃሉ ተብሎ ይጠበቃል።

ፓርቲዎቹ እንዳሉት ሰልፉ በተያዘለት ፕሮግራም ከተካሄደ፤ ከስድስት ዓመታት በሁዋላ በኢትዮጵያ የሚደረግ የመጀመሪያው የተቃውሞ ሰልፍ ይሆናል ተብሎአል።

## የኢትዮጵያ ወጣቶች 2004 የለውጥ አመት ይሆናል ማለታቸው ተዘገበ

ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ መጥቶ ጫፍ ላይ የደረሰው የኢትዮጵያዊያን የመከራ ዘመን ማብቂያው 2004 ዓም ሊሆን እንደሚገባው በተለያዩ የሃገሪቱ ክፍሎች የሚገኙ ወጣቶች ገለጹ። ዘጋቢዎቹ ከየስፍራው አሰባስበው የላኩትን ሪፖርት ዋቢ በማድረግ የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት እንደዘገበው የኢትዮጵያዊያን መከራ ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ይወገድ ዘንድ ወጣቶቹ 2004 ታሪክ ሳይሰራበት እንዳያልፍ ከፍተኛ ምኞት እንዳላቸው ገልጸዋል።

ኢሳት በዘገባው ላይ እንደገለጸው በአረቡ አለም የታዬው ለውጥ፣ በትዮጵያም ይመጣል ብለው የሚተማመኑት ወጣቶች የፖለቲካ ደርጅቶችን መመሪያ ሳይጠብቁ በራሳቸው ለመነሳሳት እንደሚፈልጉም መግለጻቸው ታውቋል።

በኢትዮጵያ የተለያዩ ከተሞች ለሚገኙ የኢሳት ዘጋቢዎች አስተያየታቸውን የሰጡ ወጣቶች ለውጥ የሚፈልጉበትን ምክንያት እንዲያስረዱ ተጠይቀው ብዙዎች፣ ኑሮውን፣ ስራ አጥነቱን፣ የመብት አፈናውንና በየጊዜው እየሰፋ የሚሄደውን የሀብታሙንና የደሀውን ልዩነት ጠቅሰዋል። በሃገሪቱ ደቡብ ክፍል የሚገኙት ወጣቶች በአብዛኛው ረሀቡንና ስራ አጥነቱን በዋና ምክንያትነት ሲያቀረቡ፣ በኦሮሚያ የሚገኙት ደግሞ የመብት አፈናውን በዋናነት ጠቅሰዋል።

በሌላም በኩል የአዲስ አበባ ወጣቶች በርካታ ችግሮችን ሲዘረዝሩ፣ ደጋግመው የሚጠቅሱት ግን ወያኔ ኢህአዴግ የአዲስ አበባን ህዝብ በምርጫ 97 ለደረሰበት ሽንፈት እየተበቀለና እየቀጣው መሆኑ የሚገልጽ ነው የሚል መሆኑ ታውቋል።

በተመሳሳይ መልኩ በአማራ ክልል የሚገኙ ወጣቶች ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ የኑሮ ውድነቱና ስራ አጥነቱ ወሳኝ ለሆነው ፍልሚያ እንደሚያነሳሳቸው ተናግረዋል ። ምንም እንኳ ወጣቶቹ የተለያዩ ምክንያቶችን ቢጠቅሱም፣ ሁሉም ግን ለውጥ እንደሚፈልጉና ለውጡም በያዝነው አዲስ አመት እንዲሆን እንደሚመኙ ለኢሳት ዘጋቢዎች ገልጸዋል።

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ የስልጣን ወምበርን ከተቆናጣጠበት ጊዜ ጀምሮ ለሃያ አመታት ኢትዮጵያዊያንን ወደ ባሰ አዘቅትና ጨለማ እየወረወረ እንደሆነ እጅግ በርካቶች የሚስማሙ ሲሆን ከዚህ መከራና ስቃይ መላቀቂያ መንገዱ አንድና አንድ ብቻ ነው፣ ይሄውም፣ የዘረኛውን አገዛዝ ከስሩ ነቅሎ መጣል በማለት አጥብቀው ይመክራሉ።

## በጋዜጠኞች ስደት ኢትዮጵያ የቀዳሚነቱን ስፍራ እንደያዘች ነው፣ ከምርጫ 97 በሁዋላ ወደ 50 የሚጠጉ የአገዛዙ ጋዜጠኞች ለስደት ህይወት መዳረጋቸው ታወቀ

በስደት የሚገኘው የኢትዮጵያ ነፃ ፕሬስ ጋዜጠኞች ማህበር ኢነጋማ ያሰባሰበው መረጃ እንደሚያመለክተው፣ በጋዜጠኞች ስደት ኢትዮጵያ የቀዳሚነቱን ስፍራ አሁንም እንደያዘች ሲሆን፣ ከምርጫ 97 በሁዋላ ወደ 50 የሚጠጉ የአገዛዙ ጋዜጠኞች ለስደት ህይወት መዳረጋቸው ተገልጿል።

እንደ ነጻ ፕሬስ ጋዜጠኞች ማህበር መረጃ በአጠቃላይ 155 የኢትዮጵያ ጋዜጠኞች በስደት ላይ የሚገኙ ሲሆን፣ ከነዚህ መካከል 106ቱ ቀደም ካለ ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ ለስደት የተዳረጉ የነፃው ፕሬስ አባላት፣ቀሪዎቹና 49ኙ ደግሞ ከምርጫ 97 ወዲህ ለስደት የተዳረጉ የአገዛዙ ጋዜጠኞች መሆናቸው ታውቋል።

በኢነጋማ ይፋ የሆነው ይህ መረጃ እንደሚያመለክተው፣ምርጫ 97ትን ተከትሎ ለስደት የተዳረጉት የዘረኛው አገዛዝ ጋዜጠኞች፣ በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት፣ በኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት፣ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎትና በራዲዮ ፋና ውስጥ ሲሰሩ የነበሩ ናቸው።

ብዙዎቹ ለስደት የተዳረጉበት ዋነኛ ምክንያትም፣ በምርጫ 97 ወቅት" አሳይታችሁዋል" በተባሉት ለዘብተኛና ቅንጅታዊ አቋም ከበላይ ሀላፊዎቻቸው ጋር ግጭት ውስጥ በመግባታቸውና - ይህንኑ ተከትሎ የደም አፍሳሽ አገዛዝ አገልጋይ ሆኖ ለመቀጠል ባለመፈለጋቸው እንደሆነም መረጃው አመልክቷል።

በአፋኝና በጨቋኝ ህጎች ወደ ወህኒ በመወርወር፣ በማንገላታት፣ በዛቻ፣ በማስፈራራት፣ በድብደባና በሌሎችም የማዋከቢያ መንገዶች ጋዜጠኞችን ለስደት ህይወት በመዳረግ ኢትዮጵያ ከዓለም የመጀመሪያዋ መጥፎ አገር እንደሆነች፣ ዓለማቀፉ የጋዜጠኞች መብት ተንከባካቢ ድርጅት -ሲ.ፒ.ጄ በቅርቡ ያወጣው መረጃ ያመለክታል።

በአሁኑ ጊዜም፣ ሁለት የስዊድን ጋዜጠኞችን ጨምሮ አምስት ጋዜጠኞች በአረመኔው መለስ አገዛዝ የሽብርተኝነት ክስ ተመስርቶባቸው በእስር ላይ እንደሚገኙ ይታወቃል።

## የአዲሱ ዓመት በአል በሚሊየኖች ለሚቆጠሩት ኢትዮጵያዊያን ታሳቢ ሆኖ አለፈ

በሚሊየኖች የሚቆጠረው ኢትዮጵያዊ ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ባመጣበት ከፍተኛ የኑሮ ውድነት የተነሳ በአሉን ለማክበር እንዳልቻለ ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ ባስተላለፈልን ዘገባ አመልክቷል።

እንደዘጋቢያችን ሪፖርት ከጥቂት አመታት በፊት ቢያንስ ዶሮ እንኩአን ገዝቶ በአሉን ማክበር ይችል የነበረው አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል በያዝነው አዲስ አመት የዶሮ ዋጋ 150 ብር በመድረሱ ይህን ገዝቶ እንኩአን በአሉን ማክበር ህልም እንደሆነበት ገልጸዋል። በዚህም ምክንያት በርካቶች በአሉ ተከብሮአል ከማለት ይልቅ ታስቦ ዋለ ቢባል ይሻላል በማለት ሲናገሩ መሰማታቸው ታውቋል።

አዲሱን አመት ተከትሎ በሚታየው ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ እጅግ እየተማረረ ያለው በሚሊየኖች የሚቆጠርው የህብረተሰብ ክፍል፣ በኢትዮጵያዊያን በተለየ ድምቀት የሚከበረውን የዘመን መለወጫ በአል ማክበር ባለመቻሉ ከመቼውም ጊዜ በላይ በሃዘን ተኮማትሮ እንደሚገኝ ታውቋል።

ዘጋቢያችን እንደገለጸው በአዲስ አበባ ከተማ ለእርድ የሚውሉ እንስሳት ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ የጨመረ ሲሆን አንድ በግ እስከ አምስት ሺህ ብር ዶሮ ከ 150 ብር በላይ፣ እንዲሁም በሬ እስከ ሃያ ሺህ ብር ድረስ መሸጡ ታውቋል።

በተመሳሳይ መልኩ በርበሬ በኪሎ ከ100 ብር ጀምሮ ፣ ቂቤ ደግሞ ከ120 ብር ጀምሮ የተሸጠ ሲሆን እንደ ባህርዳር ባሉ የክልል ከተሞች ዶሮ እስከ 120 ብር፣ በግ እስከ 1800 ብር፣ ቅቤ እስከ 90 ብርና በርበሬ እስከ 80 ብር በኪሎ ሲሸጡ እንደነበር ዘጋቢያችን ገልጸዋል።

ከዘመን መለወጫ በአሉ ጋር በተያያዘ ስላለው የኖሮ ውድነት ዘጋቢያችን ያነጋገራቸው አንዳንድ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ይሚገኙ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ለዘጋቢያችን በሰጡት አስተያየት፣ እኛ ችግራችንን ብናወራና ብንናገር ሰሚ አላገኘንም፣ ወያኔም የባሰውኑ ወደ ችጋር መቀመቅ እየገፋን ነው ያለው።በመሆኑም ይህ አዲስ አመት ከሞታችን ወይንም ከህይወታችን አንዱን የምንመርጥበት ጊዜ በመሆኑ ኢትዮጵያዊያን ልዩነታችንን አስወግደን በዚህ የወያኔ አገዛዝ ላይ የምንነሳበት አመት ሊሆን ይገባዋል ብለዋል።

## በመስከረም ወር አዲስ አበባ ውስጥ የደረሰውን ፍንዳታ

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ዊኪሊክስ ይፋ ባደረገው በዚህ ሪፖርት የተቀነባበረው ፍንዳታ ባዲስ አበባ ከተማ በደረሰበት ወቅት ዶ|ር መራራ ጉዲና ፍንዳታውን ያቀነባበረውም ሆነ ያፈነዳው ራሱ የወያኔ አገዛዝ ነው በማለት ቃለ ምልልስ ማድረጋቸውን ጨምሮ ገልጾአል።

ኢትዮጵያን ለማጥፋት ቆርጦ የተነሳው የወያኔ አገዛዝ በተለያዩ የሃገሪቱ ክልሎች ከተሞች የተለያዩ ፍንዳታዊኦች እንዲደርሱ ያደረገና በፍንዳታዎችም ሰበብ በርካታ ንጹሃን ዜጎችን እስር ቤት በማጎሩ የሚታወቅ ሲሆን፣ ኢትዮጵያዊያን የወያኔን ደባና ተንኮል አበጥረው እንደሚያውቁና ሽብርተኛውም ማን እንደሆነ በግልጽ ሲናገሩ እንደኦነበር መዘገባችን ይታወሳል።

## ዘረኛው እና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ የሱዳን ፕሬዝዳንት

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ከወያኔ አገዛዝ የወጣውን ይህንን ማስተባበያ አስመልክቶ የሱዳን ትሪቡን ጋዜጣ በትናትናው ዕለት ባሳተመው ዘገባ ፤ መለስ ዜናዊ እንደፈረንጆች አቆጣጠር ጃኒዋሪ 30 2009 ከአሜርካ ውጪጉዳይ ሚንስትር የአፍሪካ ረዳት ሃላፊ ከሆኑት ከሚስቴር | Phil Carter| ፊሊ ካርተር እና በአመሪካ ስቴት ዲፓርትመንት የሱዳን ጉዳይ ዳይሬክተር ቲም ሾርትለይ |Tim Shortley | በተገኙበት አልባሽርን ከሥልጣን ለማስወገድ አሜሪካ ሁለት ዜዴዎችን መጠቀም እንዳለባት መምከሩ በዊኪሊክስ የወጣው መረጃ የሚያመለክት ሆኖ ሳለ አገዛዙ ባወጣው የማስተባበያ መግለጫ ግን በወቅቱ አዲስ አበባ የነበሩት የቀድሞ የአሜሪካ አምባሳዳር ያማማቶ የመለስን አስተያየት አዛብቶ እንዳስተላለፉ አስመስሎ ማቅረብ ጠቀሜታ የለውም ሲል ተሳልቆበታል።

ወያኔ የኢትዮጵያን ጥቅም ለሱዳን አሳልፎ በመስጠት ተቃዋሚዎች ላለፉት 20 አመታት በዛች አገር ፈጽሞ መንቀሳቀስ እንዳይችሉ ለማድረግ የቻለ ሲሆን ርዝመቱ ከ 1600 አንድ ሺህ ስድስት መቶ ኪሎሜትር በላይ የሆነ ለም መሬታችንን በገጸ በረከትነት አሳልፎ እንደሰጠ ይታወቃል።

መለስ በአንድ በኩል ለአልበሽር ወዳጅ እየመሰለ እና የኢትዮጵያን ለም መሬት አሳልፎ እየሰጠ በሌላ በኩል አልበሽርን ከሥልጣን ለማስፈንገል ሴራ የሚሸርበው በሱዳን ውስጥ ሌላ ተጨማሪ አለመረጋጋት እንዲፈጠርና በቀጠናው ብቸኛ የሰላም አስከባሪ ሆኖ ገዝፎ ለመታየት የሚያደርገው ጥረት እንደሆነ መረጃውን የተመለከቱ ፖለቲካ ተንታኞች ይናገራሉ።

በዊኪ ሊክስ መረጃ መሠረት መለስ ዜናዊ የአልበሽርን በዘር ማጥፋት ወንጀል ለአለም አቀፍ ፍርድ ቤት መቅረብ የተቃወመው በርሱ አገዛዝ ዘመን በሱማሌ ክልልና በተቀሩት የአገራችን ክፍሎች ለተፈጸመው ተመሳሳይ እልቂት እንደሚያስጠይቀው በመስጋት መሆኑን የአሜሪካ ባለስልጣናት ተገንዝበዋል።




## መልካም አዲስ አመት

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**መካከኛ ሞገድ**:- በ 358 MB, በ 837 kHz

**አጭር ሞገድ**:- በ 31 MB በ 9700 KHz

በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz

በ 49 MB በ 5980 KHz

እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:00 እስከ 2:30 ሰዓት በድጋሚም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን። **ማሳሰቢያ**:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ተልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org